OFFICE OF ADMINISTRATIVE HEARINGS
11101 GILROY ROAD, UNIT E/CLERK'S OFFICE
HUNT VALLEY, MARYLAND 21031
(410) 229-4281 ፋክስ (410) 229-4277
www.oah.state.md.us

# የግልግልና የፍትህ ሂደት አቤቱታ ጥያቄ ማቅረቢያ

## ከዚህ በታች የሚመለከትዎት ሁሉ ላይ ምልክት ያድርጉ፦

☐ ግልግል እንዲደረግ ጥያቄ እያቀረብኩ ነው። የአስተዳደራዊ ቅሬታ ሰሚ ቢሮ፣ ሌላው ወገን ግልግል ለማድረግ ከተስማማ፣ ይህ ጥያቄ በደረሰው በ 20 ቀናት አካባቢ ውስጥ ግልግሉ የሚደረግበትን ጊዜ እንደሚወስን ይገባኛል።

☐ የፍትህ ሂደት አቤቱታ እያስገባሁ ነው። አለመግባባቱን በግልግል ለመፍታት መሞከር አልፈልግም። ወገኖቹ ስብሰባውን ለመተው ካልወሰኑ በስተቀር የሕዝብ ድርጅቱ ይህ አቤቱታ በደረሰው በ 15 ቀናት[1] ውስጥ የችግር መፍቻ ስብሰባ ጊዜ የመወሰንና የመጥራት ግዴታ እንዳለበት ይገባኛል።

☐ የችግር መፍቻ ስብሰባውን መተው እፈልጋለሁ።

☐ የፍትህ ሂደት አቤቱታ እያስገባሁና አለመግባባቱን በግልግል ለመፍታት እንድንሞክር ጥያቄ እያቀረብኩ ነው።
ሌላው ወገን በግልግሉ ላይ መሳተፍ ካልፈለገ፣ የሕዝብ ድርጅቱ ይህ ጥያቄ በደረሰው በ 15 ቀናት[1] ውስጥ፣ ሁለቱም ወገኖች ስብሰባውን ለመተው በጽሑፍ ካልተስማሙ በስተቀር፣ የችግር መፍቻ ስብሰባ የሚደረግበትን ጊዜ እንደሚወስን ይገባኛል። ሁለቱም ወገኖች ግልግል ለማድረግ ከተስማሙ፣ የፍትህ ሂደት ችሎቱ እንዳይዘገይ ይህ ጥያቄ በደረሰ በ20 ቀናት አካባቢ ውስጥ የሚደረግበት ጊዜ ይወሰናል።

*ማስታወሻ፦ ወገኖቹ አለመግባባቱን በግልግል ለመፍታት ለመሞከር ከተስማሙ ወይም የሕዝብ ድርጅቱ የፍትህ ሂደት አቤቱታውን ካስገባ፣ የችግር መፍቻ ስብሰባ አስፈላጊ አይደለም።*

<u>የተማሪው መረጃ፦</u>

ስም፦ ________________________________________________

የተወለደበት ቀን፦ ______________________

አድራሻ፦ ________________________________________________

ለልጁ ትምህርት ኃላፊ የሆነው የሕዝብ ድርጅት፦ ____________________________

ተማሪው የሚሄድበት ትምህርት ቤት፦____________________________

[1] አንድ የፍትህ ሂደት አቤቱታ፣ በወቅቱ ፈቃድ ያለው የትምህርት መርሀ ግብር ውስጥ ባልተመዘገበና በማይሄድ አካለስንኩል ተማሪ ስም ከሆነ የገባው፣ ወይም መሸጋገሪያ አማራጭ የትምህርት መስጫ ቦታ ውስጥ ምደባን ወይም የገለጻ ውሳኔን የተመለከተ ከሆነ፣ የአስተዳደራዊ ቅሬታ ሰሚ ቢሮ የተሟላ ማስታወቂያ በደረሰው ጊዜ የተፋጠነ የፍትህ ሂደት ችሎት የሚደረግበትን ጊዜ የመወሰን ግዴታ አለበት። ይህ ችሎት ችሎቱ የተጠየቀበት አቤቱታ በገባበት እስከ 20 የትምህርት ቀናት ድረስ ውስጥ መከሰት አለበት። የፍትህ ሂደት አቤቱታው በደረሰ በ7 ቀናት ውስጥ የችግር መፍቻ ስብሰባ መደረግ አለበት፣ የፍትህ ሂደቱም፣ ጉዳዩ ለሁለቱም ወገኖች አጥጋቢ በሆነ ሁኔታ ካልተፈታ በስተቀር የፍትህ ሂደት አቤቱታው በደረሰ እስከ 15 ቀናት ጊዜ ድረስ ውስጥ መጀመር አለበት።

የሚመለከተው ላይ ምልክት ያድርጉ[1]፦

☐ ተማሪው በወቅቱ ፈቃድ ያለው የትምህርት መርሀ ግብር ውስጥ ተመዝግቦ እየተማረ አይደለም ወይም

☐ አለመግባባቱ የገለጻ ውሳኔን ወይም ቅጣት ባስከተሉ ባሕርዮች ምክንያት የተከሰተ የምደባ ለውጥን ይተመለከተ ነው።

<u>ጥያቄውን የሚያቀርበው ሰው፦</u>

ስም፦ ______________________________

አድራሻ (ከተማሪው አድራሻ የተለየ ከሆነ)፦ ______________________________

ስልክ፦ (ሥራ)______________________________ (ቤት)
(ሴል)____________________

ፋክስ፦ ____________________ ኢሜል፦ ______________________________

ለተማሪው ያለው ዝምድና፦ ☐ ወላጅ ☐ የሕግ አሳዳጊ ☐ የሕዝብ ድርጅት ☐ እራስ ☐ የምትክ ወላጅ

<u>ጠበቃ/ተወካይ</u> (የሚመለከት ከሆነ)፦

ስም፦ ______________________________

አድራሻ፦ ______________________________

ስልክ፦ ____________________ ፋክስ፦ ____________________

ኢሜል፦ ______________________________

ለሚከተሉት ጉዳዮች ሁኔታን ማመቻቸት አስፈላጊ ነው (እባክዎን በትክክል ይናገሩ)፦

☐ የውጪ ቋንቋ አስተርጓሚ፦ ____________________ *(ቋንቋውን ይግለጹ)* ☐ ልዩ መግባቢያ፦ ____________________ *(ይግለጹ)*

☐ መናገር የሚሳናቸው የሚግባቡበት የምልክት ቋንቋ አስተርጓሚ ☐ ለአካለስንኩል ልዩ ሁኔታ ማመቻቸት፦ ____________________ *(ይግለጹ)* ☐ ሌላ፦ ____________________ *(ይግለጹ)*

በአካለስንኩልነት ያለባቸው ግለሰቦች የትምህርት ሕግ (IDEA) መሠረት፣ የፍትህ ሂደት አቤቱታ እያስገቡ ከሆነ፣ የችግሩን(ሮቹን) መግለጫ፣ ተገቢ ተጨባጭ ነገሮችን እንዲሁም ለችግሩ የቀረበውን መፍትሔ ጨምሮ ችሎቱ ላይ እንዲታይ ማቅረብ አለብዎት (አስፈላጊ ከሆነ ተጨማሪ ወረቀት ያያይዙ)። የፍትህ ሂደት አቤቱታው IDEA ያሳወቃቸውን አስፈላጊ ነገሮች የማያሟላ ከሆነ፣ ተቀባዩ ወገን የአቤቱታውን ብቃት አልቀበልም ማለት ይችላል።

ግልግል እየጠየቁ ከሆነ፣ ይህንን መረጃ ማቅረብ ገላጋዩን ይረዳዋል።

<u>የችግሩ(ሮቹ) ማብራሪያና ይተያያዙ ተጨባጭ ሁኔታዎች፦</u>

የቀረበው መፍትሔ ማብራሪያ፦

ስለ ግልግልና ስለ ፍትህ ሂደት ችሎቶች ተጨማሪ መረጃ ከፈለጉ፣ የሕዝብ ድርጅቱ የሰጥዎትን የሥርዓት መከላከያ ሰነድ፣ ግልግልን በተመለከተ ባብዛኛው የሚጠየቁ ጥያቄዎች የወላጅ መምሪያን፣ ወይም የፍትህ ሂደትን በተመለከተ ባብዛኛው የሚጠየቁ ጥያቄዎች የወላጅ መምሪያን ይመልከቱ። የነዚህ ሰነዶች ግልባጮች የሚገኙት ከ MSDE ዌብሳይት www.marylandpublicschools.org ላይ፣ ለልጁ ትምህርት ኃላፊ የሆነው የትምህርት መርሀ ግብር ውስጥ ያለውን የልዩ ትምህርት ዋና ሥራ አስኪያጅ ቢሮን በመገናኘት፣ ወይም የሜሪላንድ ስቴት የትምህርት ክፍል የሆነውን የልዩ ትምህርት ክፍል/ቅድመ ጣልቃ ገብነት አገልግሎቶችን በመገናኘት ነው። በይበልጥ መረጃ ለማግኘት የሚመለከቱትን የፌዴራልና የስቴት ሕግና ደንቦችን ማየት ይፈልጉ ይሆናል።

**የዚህን የግልግልና የፍትህ ሂደት አቤቱታ ጥያቄ ማቅረቢያ ፎርም ግልባጭ ለተቃራኒ ወገኑና ለአስተዳደራዊ ቅሬታ ሰሚ ቢሮ ማስተላለፍ አለብዎት።**

የአመልካቹ ፊርማና ቀን

OAH-CO-E69 doc 75489 (Revised 10/2007)

